# እምቢኝ አረፋውን!

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ይህችን የዛሬዋን ወግ በጥሞና ለማዳመጥ መተከዣ ቢጤ ከአጠገባችሁ ቢኖር መልካም ነው። ወዲያውም ከአገር ልጅ ጋር ጨዋታ የሚያምረው በወግ መካከል አለፍ አለፍ እያሉ እጅንና አፍን ማገናኘት ሲቻል ነው። አዎ የዲንሾን ቆሎ፣ የቦቅጅን ጨጨብሳ፣ የአዲግራትን አምባሻ፣ የመሐል ሜዳን ዳቦ፣ የኮረምን በሶ እንደ ቡራኬ እየተቋደሱ፤ የእነማይን ዘመራ፣ የደንበያን ጠላ፣ የጎዛምንን ዳግም-አረቄ፣ ያዲሳባን ሻይ፣ የደንቢደሎን፣ የሀረርን፣ የጎሬን፣ ወይም የይርጋጨፌን ቡና ደግሞ እንደ ጸበል ሳብ እያደረጉ የአገርን ወግ ሲያወጉ እንኳንስ አድባሩን፣ ቀየውን፣ መንደሩንና አገሩን ፈጣሪንም ደስ ይለዋል። እነዚህን ለማግኘት ያልታደላችሁ የኔ ቢጤ ስደተኞች ደግሞ ያው እንደተለመደው የራሳችሁን ቡና በቅመም እየከሸነ አምጣ ድገም እያሰኘ እንደ ማግኔት ወደሚስባችሁ ስታር በክስ (StarBacks) እጃችሁን በኪሳችሁ ከታችሁ እየተጎማለላችሁ ጎራ በሉ።

ነገሩ እንደዚህ ነው። ታሪኩን የምታውቁ ብትኖሩም ደግማችሁ ስሙት። እኔም ነፍስ ካወኩበት ጊዜ ጀምሮ ደጋግሜ ብሰማውም አልሰለቸሁትም። ድሮ ድሮ (ገና ለገና አፋጦ እሚጠይቅን ዜጋ ግንባር የሚመታ ሰራዊት የለውም ብላችሁ “መቼ?” ብላችሁ ገና ከጅምሩ በጥያቄ አትወጥሩኝ። እኔም ይህንን ጥያቄ አያቴን ጠይቄው የመለሰልኝ መልስ “እኔንም አያቴ ያጫወተኝ ድሮ ድሮ እያለ ነበርና ዝምብለህ አዳምጠኝ!” የሚል ነበር።) እና ድሮ ድሮ በአንድ ላይ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ያው እንደምታውቁት በባህላችን መሰረት ይህቺ የተከበረች ሚስት ስትታጭ የባል ወገኖች የራሳቸውን የአጥንት ጥራት፣ የልጁን ቁምነገረኛነትና ጀግንነት አስረድተው፣ ዋሽተው የሚያገናኙን ሳይሆን ከእውነት ጋር ቃል-ኪዳን ያላቸውን አንደበተ-ርቱዕ ሽማግሌዎች ልከው፣ ብዙ ጊዜ ተመላልሰው ጉልበት ስመው የታጨችዋን ልጃገረድ ተረከቡ። ከዚያም ጥምጣሞቻቸውን እንደ አውሎ ነፋስ ሽቅብ ቀጥ አርገው ያቆሙ ካህናት ጽዋቸውን ጨብጠው “ወይን ያስተፌስህ ልበ ሰብ” በሚል መርህ ጠላና ጠጃቸውን የሚኮመኩቡበት፤ ከነሱ ጎን ለጎን ደግሞ ጺማቸውን ያንዠረገጉ ሼሆች ቢስምላሂ ብለው እየባረኩ ጮማቸውን የሚቆርጡበት፣ አንቱ የተባሉ ያገር ሽማግሌዎች እንደዚሁም ተራው ሕዝብ በዳስ ውስጥ ተሰብስቦ እምብርት እስቲያብጥ ድረስ እየበላና እየጠጣ የሚደስትበት ድል ያለ ሰርግ ተደገሰ። ይህ የሰርግ ሥርዓት ሃይማኖታዊም ሆነ መልከ-ምድራዊ ክልል-አልባ በመሆኑ አምላክን ሳይቀር ይበል ያሰኝ ነበር ይባላል።

አሳላፊዎች ጠላውንና ጠጁን በዋንጫና በብርሌ አፍ ውስጥ እያንቆረቆሩ ከላይ ታች በሚሉበት ሰዓት የጋብቻውን ስምረትና የድግሱን መልካምነት የሚጠቁሙ ቅኔዎች ተቀኝተውና ዜማዎች ተደርድረው፤ “ትዳራቸውን ይባርክ፤ የእቧይ ዘር የፌደል ዘር ያድርጋቸው፣ አገር ይባረክ! አገር ይቀደስ! አገራችን ጠቢያን ፈጣሪ ይጠብቃት! እየተባለ በአገሪቱ ውስጥ ላለው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት፣ ለተክሎች እንደዚሁም ለወንዙ፣ ለተራራው፤ ለሸንተረሩ፣ ላፈሩ ለጠጠሩ ሁሉ ምርቃት ተዘከረ። ቀጥሎም ሙሽራው ለሙሺሪቱ ያመጣው ስጦታ ከተቆጥረ በኋላ “አናስገባም በሩን”*(“ካላስገባችሁን እንመለሳለን” ቢሉ የሚሆነውን አላውቅም)* እያለ የሚከለክለውን የሙሽሪት ዘመድ ሰንጥቆ በመግባት ሰርገኛው ሙሺሪቱን በጁ ውስጥ አስገባ። አዎ እንደ ወጉ ሁሉ በሆታ በእልልታ ሙሽሪቱን ተሸፍና ከተቀመጠችበት ቤት አውጥተው ደጅ ድረስ በጀርባ ተሸክመው ከዚያም በኮርቻና በግላስ ከተሽቆጠቆጠ ፈረስ ላይ ጉብ አርገው እርሷ እያለቀሰች *(ጥርሳቸው የቀለም ደን የለበሰውን ከንፈራቸውን እንደ ጦር በርቅሶ ለሚወጣው የአሁን ዘመን ሙሽሮች ይህ እንግዳ ሊሆን ይችላል)* ሰርገኞች ግን “እምቢ በል” (አሁን አሁን “እሽ በል” በሚል የተተካ ይመስላል) የሚለውን ሆታ እያቀለጡ ወደ ሙሽራው መንደር ነጎዱ። ወንዙን ተሻግረው አቀበቱን ወጥተው ከሙሽራው ቤት ሲደርሱ ጠላትን በገፍ እንደማረከ ሰራዊት በኩራትና በደስታ መንፈስ ከድሮውም የበለጠ ሆታውን አቅልጠው ከጨፈሩ በኋላ እንባዋ የደረቀውን ሙሽራ ከፈረስ አውርደው እንደገና ሚዜዎች በጀርባቸው ተሸክመው ከሙሽራው ቤት ይዘው ገቡ።

የሰፈሩ ሕዝብ ምሽቱን ሁሉ በደስታ ሲጨፍር አመሸ። ከዚያም የደከሙት የመንደሩ ሰዎች አንድ በአንድ መሰስ እያሉ ሲሄዱና ዘመድ አዝማድ ሲቀር “የቤተ-ዘመዱ ሊታይ ነው ጉዱ” እየተባለ ሲጨፍር፤ ዘወር ወዳለው ቦታ ደግሞ እንደ ደንብ እንደ ልማዱ ሁሉ ሙሽራው ሕግን አድርሶ ብር አንባር ሰበረልሽ ሲባል ሁሉ አለም በሰላምና በደስታ ተሞልታ ነበር። እንዲያውም ለቀጣይ ሁለት ወራት ያህል ሙሽሪቱ መቀነቷን እስከምትፈታ ድረስ ከመደብ ላይ ጉብ ብላ ፀሐይ የሚባል ነገር ሳይነካት እየዋለች፣ ሙሽራው እንደዚሁ ሙሽራ ነው እየተባለ ጠንከር ያለ ስራ ሳይሰጠው፣ ሁለቱም እንደ አራስ ምርጥ ምርጡ ምግብ እየተዘጋጀ እየተሰጣቸው ሲሞሸሩ ባለበት ወቅት ኑሮ የተሟላች፣ በጎ፣ ፍንትው ያለች፣ ውብና ያማረች ነበረች። እንዲያውም “ኩርኩም፣ ፏደሬ፣ ገበጣ፣ ወዘተ የሚባሉት የጫጉላ ጨዋታዎች የሙሽርነታቸውን ወቅት ውበትና ለዛ ያደምቁት ነበር። የሙሽራው ሚዜዎች እንደዚሁም አንዳንድ ፍቅራቸውን ለመግለጽ የፈለጉ ወዳጆችና ዘመድ

አዝማዶች ዶሯቸውን እያረዱ፣ እንጎቻ እያነጎቱ፣ ፍትፍታቸውን እየፈተፈቱ፣ ጠላቸውን እየጠመቁ ጫጉላን እውነትም ጫጉላ አሰኝተዋት ነበር።

መቼም ሁሌ ሙሽራ መሆን አይቻልም። የሚቻል ቢሆንማ ኖሮ ሰው ሁሉ የዘላለም ሙሽራ ለመሆን ገንዘቡን ሁሉ ስለት በማስገባት ይጨርስ ነበር። እውነቴን ነው እስቲ ሁሌ እንደ ሙሽራ ክብር ያለው ሰው ለመሆን የማይሻ እጁን ያውጣ!  እንደ አገረ ገዥዎች በጡጫ ተገዶ ሳይሆን በእውነተኛ ፍቅርና አክብሮት ሕዝብ "ሙሽራዬ…ን" እየዘመረ የሚሰግድላቸው ሙሽሮችን መሆን የማይሻ ማን አለ? ወንበር ላይ ለመውጣት ከንቱዎች ደም እንደ ጅረት በሚያፈሱበት አገር በታላቅ ክብርና ፍቅር ተሸክመው ከወንበርም ከሚረዝመው ፈረስ ላይ የሚሰቅሏትን ሙሽራ ክብር መውረስ የማይሻ ማን አለ? በሰፈሩት ቁና ይሰፈራል እንደሚባለው አረመኔ ገዥ ከተቸከለበት ወንበሩ እንደ እርጥብ የበሬ ቆዳ በሐይል ተዥልጦ በሚወርድበት አገር በክብርና ከልብ በመነጨ ፍቅር እንደ እንቁላል ተንከባክበው ከፈረስ ላይ አውርደው ዙፋን ላይ የሚያስቀምጧትን ሙሽራ መሆንን የማይፈልግ ዜጋ ማን አለ? ድሆች ሳይወዱ ተገደው ከጉረሯቸው እየሞለቀቁ እንዲያውም ሰማቸውንም መለመኛ እያደረጉ በእርጥባን ገንዘብ ገዳይ ገዥዎቻቸውን በሚቀልቡበት አገር ከልብ በመነጨ ደስታ ተውጠው ቤታቸው ያፈራውን ምርጥ ምርጥ ምግብ የሚያበሏት፣ በተዋበ ድሪ፣ ጠልሰምና አልቦ የሚያሽቆጠቁጧትን፣ በናፍቆት እምቧ እያሉ ጉንጯን የሚስሟትን ሙሽራን መሆን የማይሻ ማን አለ? ታዲያ የሙሽርነት ደካማ ጎኑ ጊዜአዊ መሆኑ ነው። አዎ ሙሽርነትም ጊዜአዊ ነውና የእነዚህ ሙሽሮች የሙሽርነት ዘመንም አለፈና ሁለቱ ሶስት ጉልቻ የሚፈጥሩበት ወቅት ደረሰና ጎጆ ወጡ።

በድሮው ዘመን ሙሽርነት ከወላጅ ጋር አብሮ ከመኖር ወደ ራስን ችሎ መኖር መሸጋገሪ ድልድይ ነበር። በዚህም መሰረት እነዚህ ሙሽሮች ይህንን ድልድይ ተሻገሩና የኑሮን አቀበት እየተፍጨረጨሩ መውጣት ጀመሩ። ሙሽሪት መደብ ላይ ጉብ ብላ ኩል በሚኩሉ፣ ጣት የሚያስቀረጥም ምግብ በሚያዘጋጁ፣ "አፈር ስሆን" እያሉ በሚያጎርሱ ወይዛዝርት እየታጀበችና እየተንቀባረረች መዋሏ እንደታሪክ ወደ ኋላ ቀረና የወር ጨው (አስቤዛ) ማዘጋጀቱ ከከንዷ ላይ አረፈ። ሙሽራውም በእናትና በአባት ሐሳብ እየተንደላቀቁ መኖር አከተመና ያችን ሁለቱን ሸፍና የያዘችውን ጎጆ የማስተዳደር ቀንበር በጫንቃው ላይ ወደቀበት። ያችን ጣራ ተከልለው፣ በራቸውን ገርብበው፣ በአንድ ሞሰብ በልተው፣ በአንድ ቅል ጠጥተው የሚኖሩ ሰዎች ሁለቱ ብቻ ሆኑና ቁጭ አሉ። በሙሽርነት ዘመን የተዋወቁት ገላ-ለገላና ወዝ-ለወዝ ብቻ ነበር። አሁን ብቻቸውን ሲኖሩ ግን አመል-ለአመል፣ ባህሪ- ለባህሪ መተዋወቅ መጣ። እንደምታውቁት የጎጆ ነገር እንኳን ለጀማሪ ለዘማርም አስቸጋሪ ነው። እርግጥ ነው የጎጆ ጣጣ ሲጀምር እንኳን የተደበቀንና ያለን የሌለንም አመል ያስወጣል። በመሆኑም እየዋሉ እያደሩ በሄዱ ቁጥር እነዚህ የትዳር ጓደኞች የተደበቁና አዳዲስ አመሎች ማውጣት ጀመሩ። ሶስት ጉልቻ ለማቆም የጀመሩበት ወራት በጨመረ ቁጥር የሚያሳዩት የአመል መጠንም እየናረ ሄደ። አንባቢ እናቶቼና እህቶቼ "የወንዶች ነገር" ብላችሁ ወጉን አታጣጥሉትና (ይህንን አይነት ባህሪ ያለን ባሎችም አያሌ ነንና) የሚስቲቱ እንግዳ አመል እጅግ እየበረታና እጅ እግር የሌለው እየሆነ መጣ። ለምሳሌ ያህል ብርሃን ሲል ጨለማ፤ ጥቁር ሲል ደግሞ ነጭ ትላለች። ወደ ሰሜን ሲያመለክት እርሷ ወደ ደቡብ ትጠቁማለች። ነገሯ ሁሉ ቁጭ እንበል ሲል እንቁም፤ እንተኛ ሲል እንሂድ፤ እንብላ ሲል እንጹም፤ እንዝፈን ሲል እናልቅስ ወዘተ ሆነና አረፈው። ሌላው ቀርቶ ቆንጆ ነሽ እያለ ሊያንቆለጳጵሳት ሲሞክርም በምሬት "እምቢዬው አስቀያሚ ነኝ" ትልና እውነት አስቀያሚ ለመምሰል ከንፈሯን አዘናንፋና አጨማዳ ቁጭ ትላለች።

"ለእኛ ትነግረናልህ!" ብላችሁ አትሳለቁብኝ እንጅ የኑሮ ጎዳና እንደሁ እንኳን በተቃራኒ አቅጣጫ እየተራመዱበት እጅ ለእጅ ተያይዞ እየተጓዙበትም ቀጥ ያለ መስመር አይዝም። ይህም በመሆኑ የእነዚህ በተለያዬ አቅጣጫ መራመድ የጀመሩት ባልና ሚስት ኑሮ አንድ ስንዝርም ወደፊት ሊራመድ አልቻለም። አዎ ለጎጆ መውጫ የተሰጧቸው ሶስቱ ጉልቾች እንኳን ቀጥ ብለው ሊቆሙ በዚህ ሁኔታ ምድጃ ውስጥም አንገባ ብለው አመጹ። ጠላታችሁ ቅዝቅዝ ይበል(አሜን በሉ)! እንኳን ቤቱ ምድጃውም እንደ በረዶ ቀዘቀዘ። በዚህ ግራ የተጋባው  አቶ ባል የሆነ ምስሎት ቋንቋውን ቀይሮ በተቃራኒ የመናገር ስልት ፈጠረ። መሄድ ከፈለገ እንተኛ፣ መብላት ከፈለገ እንጹም፣ መቆም ከፈለገ እንቀመጥ፣ ምስራቅን ለማሳየት ከፈለገ ወደ ምእራብ እያመለከተ፣ ቆንጆነቷን ለመግለጽም አስቀያሚ የሚለውን ቃል እየተቀመ ኑሮን ትንሽ ወደ ፊት ፈቀቅ ለማድረግ ሙከራ አደረገ። ዳሩ ግን አንድ በሬ ጠምዶ እንዴት ማረስ ይቻላል? በአንድ ጉልቻ ምን ይጥዱል? በአንድ ባላስ እንዴት ዘሃ ይዘጓል? ካለ ወጋግራ፣ ግድግዳና ማገር ባንድ ምሰሶ ብቻ እንዴት የቤት ጣራ መስቀል ይቻላል?

ብዙዎቻችሁ እንደምትገነዘቡት አብዛኛውን ጊዜ የሚስት ወላጆችና ዘመዶች እንቁጣጣሽ፣ መስቀል፣ ገና፣ ፋሲካና የፍስለታ ግድፍት በመሳሰሉት የባእል ቀኖች አብረው ለማዋል ልጆቻቸውን ከነባሎቻቸው ደግሰው ይጠራሉ። በዚህ ደንብ መሰረትም እነዚህ የተጋቡት ወጣቶች ለፍልሰታ ግድፍት ከሚስቲቱ ወላጆች ጋር አብረው በአሉን እንዲውሉ ተጠሩ። መቼም የጌጥ አይነት ከሚታይባቸው አጋጣሚዎች አንዱ አምቻ(የልጅ ባል) ለመጀመሪያ ጊዜ አማቶቹን ሲያይ ምራትም(የልጅ ሚስት) ለመጀመሪያ ጊዜ አማቶቿን ለማየት ሲዘጋጁ የሚያጌጡበት ወቅት ነው። በዚህ ቀን አቶ ባል የክት ልብስ የሚላትን ዳርዳሯ በቀለማም ክር የተዋበችን ሙታንታውን በቀበቶ ጠስቆ፤ በዚያ ላይ ቦግ ቦግ ያለ ኪስ ያለውን ኮቱን ግጥም አድርጎ፤ ከዚያ በላይ ደግሞ በእንዶድ እብድ እስቲል የታጠበውን ጋቢውን አጣፍቶ፤ ግራና ቀኝ የወረደውን የጋቢውን ክፍል ሰብስቦ

በትክሻዎቹ ላይ አስቀምጦ፤ በቅባት የወዛ ዱላውን በቀኝ እጁ ከቀኝ ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ፤ በግራ እጁ ደግም የጋቢውን ጠርዝ ከአፍንጫው ላይ ጣል አድርጎ፤ ከዚያም ሽበላ ጎበዝ መኖኑን ጥላውን በማየት አረጋግጦ፤ በሌጣ እግሩ ወደ አማቶቹ አገር ጉዞ ጀመረ። ሚስቲቱ እንደዚሁ ጠጉሯን በእንጨት ሚዶ ነቃቅሳና አደስ በጎረሰ ቅቤ አውዝታ፤ ራሷን ዙሪያውን በባውንድ(ሻሽ) አስራ፤ በጥልፍ ያማረውን ቀሚሷን ዳርዳሩ በተለያዩ ቀለማት በተሽቆጠቆጠ መቅነት ሸክፋ፤ በዚያ ላይ ያማረ ነጠላዋን ጣል አድርጋ፤ እንደ መዛግ ያለች ክብ መስታዎትዋን ከሙዳይዋ አውጥታ፤ ፈገግ-ቆጣ፣ አይኖቿን ክፍት-ክድን፣ አንገቷን መለስ-ቀለስ እያደረገችና ፊቷን በአንባሬ ጭቃ እያወዛች ደጋግማ አይታ፤ ኮራ ያሉ ዳሌዎቿን እንደዚሁ መቃ አንገቷን በትከሻዎቿ እያሻገረች ፊርጠም እያለች ተመልክታ፣ ጥላዋን በቀኝ እጇ ዘርግታ በልጃገረድ ሳይሆን አሁን በተማረችው የወይዘሮዎች አካሄድ ወግ እርምጃዋን እየሰፈረች በአልቦ በተዋቡ እግሮቿ ሳብ-ረገድ ሳብ-ረገድ እያለች ከባሏ ኋላ-ኃላ ጉዞዋን ቀጠለች።

ሐምሌና ነሐሴ አባይ፣ አዋሽ፣ ባሮ፣ ገናሌ፤ ዋቢ ሸበሌ፣ መረብና ተከዜ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ወንዞችና ጅረቶች አፍር ጎርሰውና ጎልበተው በጀብደኝነት እየተጥመለመሉ የሚፈሱባቸው ወሮች መሆናቸው የታወቀ ነው። እንደምትገነዘቡት የፍልሰታ ግድፍት የሚውለው ደግሞ በነሐሴ ወር ነው። ከሚስቲቱ ዘመዶች አገር የሚደረሰው በክረምት እንደ ዝሆን የሚግበሰበስና እንደ አንበሳ የሚያገሳ ወንዝን ተሻግሮ ነበር። ባልና ሚስት ተደግሶ የሚጠብቃቸውን ድግስ እያሰቡና ልክ አጠገባቸውን እንዳለ ሁሉ በአፍንጫቸው እያሸተቱና በምላሳቸው እያጣጣሙ እንደዚሁም ሲደርሱ በቀኝ የሚጣለውን ላታማ ሙክት በናላቸው እያወጡ-እያወረዱ ሲጓዙ ይህ ድልድይ-አልባ ወንዝ ከመጠን በላይ ጢም ብሎ እያጓራ ሜዳውን ሳይቀር አልብሶት አገኙት። ደግነቱ አቶ ባል የተዋጣለት ዋናተኛ ከመሆኑም ባሻገር የዚህን ወንዝ አመል በሚገባ ያውቀው ነበር። እንዲያውም "ተዋፉ ላይቀር እንደ እንተና (ስሙን እየጠሩ)!" እያሉ የሰፈሩ ልጃገረዶች የዚህን ወንድ ጉብዝና በፍቅር መልክ እያነሱ ሚስቲቱን ሊያስቅኗት ይሞክሩ ነበር።

ይህ ወንዝ በሚሞላበት ወቅት ስንቱን እየተሸከመ በማሻገር የሚታወቀው ይህ ቆፍጣና ባል ባለቤቱን "ነይ ተሸክሜ ላሻግርሽ" ብሎ ይጠይቃታል። "የቤት አመል ከደጅ ይወጣል!" እንደሚባለው " ዘወር በል ከዚህ! ራሴ እሻገራለሁ!" ብላ እምቢተኝነቷን እንደተለመደው ትገልጻለች። አሁንም ባል ትንፋሹን ዋጥ አርጎ "ራስሽ መሻገር ከፈለግሽም መልካው (የሚሻለው መሻገሪያ) በዚህ በኩል ነውና በዚህ በኩል ተሻገሪ!" ብሎ ሊመክር ሞከረ። "እምቢ በዚህ ሳይሆን በዚያ በኩል ነው የማቋርጠው" ብላ አሻፈረኝ አለች። ከብዙ ልመና በኋላ ተስፋው የተሟጠጠ ባልም በሚያውቀው መልካ ሙላቱን ከቁብ ሳይቆጥር ተሻግሮ ሚስቱን ማዶ ሆኖ መጠባበቅ ጀመረ። ሚስቲቱም የቀሚሷን ግራና ቀኝ ጫፍ ወደ ላይ ስባ በመመቀነቷ ውስጥ ካስገባች በኋላ አዙሮ በመድፋት ባህሪው አዙሪት- ድንብልዝ እየተባለ በሚታወቀው የወንዙ ክፍል በኩል ለመሻገር እግሮቿን ከተተች። ትንሽ እንደተራመደች እንደፈረስ የሚጋልብ ማእበል ጠልፎ የቆመችዋን ወይዘሮ በሆዱ አስተኛት። አቶ ባል ሚስቱን ለማዳን በቅልጥፍና ዘሎ ከወንዙ ውስጥ ገብቶ "እጄን ያዥኝ! እጄን ያዥኝ!!" እያለ ሲጮህ እርሷ "እምቢኝ ውሃውን ነው! እምቢኝ ውሃውን ነው!" አለች። "እኔን መያዝ ካልፈለግሽም ጀጀባውን (ውሃ ዳር ወይም ውስጥ የበቀለ ተክል) ያዥው! …ጀጀባውን ያዥው!!" ሲላት ደግሞ "እምቢኝ አረፋውን! እምቢኝ አረ..ፋውን!!" እምቢኝ አረ..ፋ..ው…ን!!! እያለች የማይጨበጥ አረፋ እየጨበጠች ከወንዙ ጋር ሄደችና አረፈችው ይባላል።

በእንቢኝ አረፋውን የገመድ ጉተታ ወደ ፊት የመራመድ ሳይሆን ወደ ኋላ የመግደርደር እጣ ፋንታ ከገጠመው ይህ ቆፍጣና ጎበዝ እጅግ በከፋ ሁኔታ ባለሙያዋና በትልቁ መጣፍ በኤደን የተመሰለችው ጦቢያም በአመራር ውሀ ውስጥ መዋኘት የማይችሉ ነገር ግን ቅል እንኳን በጀርባቸው ሳያስሩ አይናቸውን ጨፍነው ከቤተመንግስት ባህር ውስጥ ዘለው የሚጠልቁ፤ እንደ ሙሽሪቱ ተለምነው ሳይሆን እንደሌባ በሯን በርግደው የሚገቡ ጠላፊዎች በተለያዩ ጊዜ ገጥመዋታል። ወዲያው እንደገቡ መስመጥ ሲጀምሩም "ሕዝብ" እኛን ያዙ ብሎ እጁን ሲዘረጋ "እምቢኝ ወንበሩን ነው!" እያሉ አጥንት እንደ ጎረሰ ውሻ የወንበር እግር በመንጋጋቸው እንደነከሱ የጎርፍ ማእበል ይዟቸው ይሄዳል። አዎ አላዋቂ ዋናተኞች በድርቅና ከገቡበት ባህር ውስጥ በመማቀቅ ላይ ሳሉ እንኳን "እጃችንን ወይም ጀጀባውን ያዙ!" ለሚሉ እንደ ሀዲስ አለማየሁ ላሉ ጀግና ዋናተኞች "እምቢኝ አረፋውን!" የሚል መልስ እየሰጡ የሕዝብን እድል በእጃቸው ጨምድደው እንደያዙ ጎርፍ ጠርጓቸዋል፤ ገናም ይጠርጋቸዋል። እንዲያውም ምክር አለመቀበል ብቻ ሳይሆን እነዚህ ከንቱዎች እጃችንን ያዙና ከጎርፉ ዳኑ የሚሏቸውን ጥሩ ጥሩ ዋናተኞች ወንጀል ለመፈጸም በማይታክቱት እጆቻቸው ጉርንቧቸውን ያንቁና ሲጥ ያረጓቸዋል፤ ያስሯቸዋል፤ አለዚያም ከባህሩ አካባቢ እንዳይደርሱ ያሳድዷቸዋል። በእንደነዚህ አይነት ተንኮለኛ ተንጨፏራቂዎች ምክንያት ውቂያኖስና ህዋ የሰውን ልጅ ጉዞ ባልገቱበት በሃያ-አንደኛው ክፍለ-ዘመን ሕዝበ-ጦቢያ እጅና እግሩ ታስሮ በችጋር፣ በመከራ፣ በበሽታና በእልቂት ኩሬዎች ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያለ በመማቀቅ ላይ ይገኛል። ስለዚህ ወንዝን ለመሻገርም ሆነ ከቤተ መንግስት የመዋኛ ኩሬ ውስጥ ለመዋኘት ሲሆን ሲሆን በደንብ የተካኑ ዋናተኛ መሆን፤ ሳይሆን ሳይሆን ደግም "እምቢኝ አረፋውን!" የሚባልን ጅል-አመል አስወግዶ ባህርና ወንዝን ሰንጥቆ የሚጓዝን ዋናተኛ እጅ ይዞ ለመሻገር ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። አመሰግናለሁ!

*የካቲት ሁለት ሺ ሁለት ዓ.ም.*